Contact: Public and International Relations Dept
ECCSA
Phone 251 11 5519537
Fax 251 11 5517699

Web:
www.ethiopianchamber.com

**Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations**

# Press Release

**<u>የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤቶች ጉባዔ ዝግጅት ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ (Intrim Committee) ስብሰባ ሊካሄድ ነው፡፡</u>**

በኢትዮጰያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት በመጪው ሰኔ ወር 2001 በአዲስ አበባ የሚካሄደውን የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤቶች ጉባኤ ዝግጅት እንዲያስተባብር የተቋቋመው ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ (Intrim Committee) ስብሰባውን ቅዳሜ መጋቢት 26 ቀን 2001 ያካሄዳል፡፡

የጊዜያዊ አስተባበሪ ኮሚቴ ስብሰባ መሠረታዊ ዓላማ በመጪው ሰኔ ወር አዲስ አበባ ላይ ለሚካሄደው የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤቶች ጉባኤ የውይይት አጀንዳ መቅረጽ፣ ከዚህ ቀደም የተkkመው የአፍሪካ ንግድ ፣ ኢንዱስት እርሻና የሙያ ምክር ቤት ዮኒየን ስታቲዮት (Statute) ማሻሻል ፣ ጉባኤ የሚካሄድበትን ትክክለኛ ቀን መወሰንና የሥራ መርሃ ግብር ማጽደቅ ከሚጠቀሱት ወስጥ ናቸው፡፡

የኢትዮጳያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የአገራችንን ገጽታ ለማሻሻልና ምክር ቤቱ በአፍሪካ ደረጃ ያለውን ተደማጭነት ለማጉላት የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤቶች ኮንፈረንስ በአዲስ አበባ እንዲካሄድ ተነሳሽነቱን ወስዶ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ኮንፍረንሱ ከህዳር 16 -17/2001 በተሳካ ሁኔታ መካሄዱ ይታወቃል፡፡

በዚህ ኮንፈረንስ ላይ 17 አገሮች የተሣተፉ ሲሆን በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ አንድ ጠንካራ አህጉራዊ የንግድ ምክር ቤቶች ህብረት እንዲቋቋም ከሥምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ኮንፈረንሱ የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤቶች ጉባዔ በመጪው ሰኔ ወር 2001 በአዲስ አበባ እንዲካሄድና ለጉባዔው ስኬት ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያመቻች አሥራ አምስት ዓባላት ያሉት ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲቋቋም ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ፣ ናይጄሪያ ምክትል ፕሬዚዳንትና ኢትዮጵያ ፀሐፊ የሆነችበት ይህ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ (Intrim Committee) የፊታችን ቅዳሜ መጋቢት 26 ቀን 2001 በአዲስ አበባ ስብሰባውን ያካሄዳል፡፡

For Release April 2, 2009

*more*

የጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴው ስብሰባ በመጪው ሰኔ ወር አህጉራዊ የንግድ ምክር ቤቶች ጉባዔ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በመጪው ሰኔ ወር የሚካሄደው የአፍሪካን ንግድ ምክር ቤቶች ጉባዔ ከዚህ ቀደም የተkkመው አህጉራዊ ተቋም ሁሉን ዓባል ምክር ቤቶች ባሳተፈ መልኩ ይበልጥ እንዲጠናከር ፣ ለአባል ምክር ቤቶች ተገቢውን አገልግሎት መስጠት እንዲችል ፣ ጠንካራ የግል ዘርፍ በአፍሪካ እውን እንዲሆንና አንድ የተባበረ የኢኮኖሚ ማሕበረሰብ ለመፍጠር በአፍሪካ አገሮች የተጀመረውን ጥረት ከዳር ለማድረስ መሠረት የሚጥል እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጰያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 341/95 መሰረት በአዲስ መልክ ከተደራጀበት ከ1999 ጀምሮ የተጣለበትን አገራዊ ሃላፊነት በብቃት ለመወጣት ባደረገው እንቅስቃሴ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን ያከናወነ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ከዚህ ቀደም በመንግስት ተወርሶ የነበረውን ባለ ሰባት ፎቅ ህንጻ ማስመለሱ ፣ የአምስት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረጉ፣ የምክር ቤቱን ተልዕኮ መሰረት ያደረገ ድርጅታዊ መዋቅር ተግባራዊ ማድረጉና በሰው ሃይል እንዲሟላ ማድረጉ፣የአባል ምክር ቤቶችን አቅም ለማጠናከር እንቅስቃሴ መጀመሩ ፣ የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤቶች ኮንፍረንሱ በህዳር ወር 2001 በተሳካ ሁኔታ ማካሄዱ ለአብነት ያህል የሚጠቀሱ ሲሆን በቀጣይም እንደ አገራዊ ምክርቤትነቱ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለማድረግ በመልካም ጅምር ላይ እንደሚገኝ በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡